የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 27
Addis Ababa, 5th July, 2018


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፫/፪ሺ፲**

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሣኝ ኩነት ምዝገባ፣ የነዋሪነት መታወቂያ እና ሌሎች አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ ደንብ**

**ገጽ………………….…………ሺ፬፻፶፱**


**CONTENT**


**Regulation No 103/2018**

**Addis Ababa City Government Vital Events Registration, Residents' Identity Card and Other Services Rendering Service Charges Regulation**

**Page…………………………1459**


## ደንብ ቁጥር ፻፫/፪ሺ፲

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሣኝ ኩነት ምዝገባ፣ የነዋሪነት መታወቂያ እና ሌሎች አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ ደንብ

የከተማ አስተዳደሩ ለሚሰጠው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ፣ የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች አገልግሎቶች ሲያስከፍል የነበረው ክፍያ የአገልግሎቶቹን ወጪ የማይሸፍን በመሆኑ የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆነው አገልግሎት ተቀባይ ፍታሃዊ በሆነ የአገልግሎት ክፍያ ወጪውን እንዲጋራ በማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት በማስፈለጉ፤

## REGULATION No 103/2018

## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT VITAL EVENTS REGISTRATION, RESIDENTS' IDENTITY CARD AND OTHER SERVICES RENDERING SERVICE CHARGES REGULATION

**WHEREAS,** it has found necessary to provide efficient, effective and quality services for the service receivers that directly accept the services to justly share the service delivery expenses as the service charges applied by the city government to provide the vital event registration, residents' identity card and other services did not cover the expenses of the thereof;


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ብሔራዊ መታወቂያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፲፴፱/፪ሺ፱ አንቀጽ ፪ ንኡስ አንቀጽ /፲፬/ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፩/፪ሺ፱ አንቀጽ ፲፮ ንኡስ አንቀጽ /፩/ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ፣ የነዋሪነት መታወቂያ እና ሌሎች አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ ደንብ ቁጥር ፻፫/፪ሺ፲ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የተፈፃሚነት ወሰን**

፩. ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ፣ የነዋሪነት መታወቂያ እና ሌሎች አገልግሎቶች አሰጣጥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በደሃ ደንብ የሚስተናገዱ ነዋሪዎች ላይ ተፈጻመ፣ነት አይኖረውም፡፡

**፫. ለወሣኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት ስለሚጠየቅ ክፍያ**

፩. የፌዴራል ወሣኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በአወጣው የወሣኝ ኩነት ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የኢትዮጵያ ዜጋ ለሆነ ሰው ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅነት የፀና መታወቂያ ለያዘ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ዜጋ ለሚሰጠው የወሣኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ አንድ እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with sub-article (14) of Article (2) of the Vital Events Registration and National Identity Card Amendment Proclamation No 1049/2017 and sub-article (1) of Article 16 of the Addis Ababa City Government Finance Administration Proclamation No. 51/2017, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this regulation as follows.

**1. Short Title**

This regulation may be cited as the " Addis Ababa City Government Vital Events Registration, Residents' Identity Card and other Services Rendering Service Charge Regulation No 103/2018."

**2. Application Scope**

1. This regulation shall be applicable on vital events registration, residents' identity card and other services provision in the Addis Ababa City Government.
2. Without prejudice to sub-article (1) of this article, it shall not be applicable on those residents treated as pauper.

**3. Service Charges requested for Vital Events Registration Service**

1. The service charges to be paid for the provision of vital events registration service, in accordance to the vital events registration implementation directive issued by the federal vital events registration agency, by Ethiopian citizens or a foreign citizen of Ethiopian origin that holds a permanent Ethiopian origin identity card, is specified under schedule one which is annexed with this regulation.

፪. የፌዴራል ወሣኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በአወጣው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ ዜጎች ወሣኝ ኩነት ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ የውጭ አገር ዜጋ ለሚሰጠው የወሣኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ሁለት እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

**፬. የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ**

፩. ፀንቶ በሥራ ላይ ባለው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ምዝገባና የነዋሪነት መታወቂያ አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ለሚሠጡ አገልግሎቶች የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ሶስት እንደተመለተው ይሆናል፡፡

፪. ለሌሎች አገልግሎቶች የሚከፈለው የአገልግሎቱ ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ አራት እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

**፭. የአከፋፈል ሁኔታ**

፩. ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት ሠንጠረዦች የተመለከቱት የአገልግሎት ክፍያዎች በተናጠል እና አገልግሎቶቹ በተጠየቁ ጊዜ መከፈል አለባቸው፡፡

፪. ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ዓይነት የሚፈፀም ክፍያ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ለየብቻ መከፈል አለበት፡፡

**፮. ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ስለመሆን**

ከዚህ የሚከተሉት አገልግሎቶች ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ናቸው፡-

2. The service charge to be paid for the provision of vital events registration service, in accordance to the implementation directive for the vital events registration of foreign citizens living in Ethiopia issued by the federal vital events registration agency, by a foreign citizen is specified under schedule two which is annexed with this regulation.

**4. Residents' Identity Card and Other Services Payment**

1. The service charges to be paid for the services rendered, pursuant to the Addis Ababa city residents registration and residents' identity card provision current directive, is specified under schedule three which is annexed with this regulation.
2. The service charges to be paid for other services are specified under schedule four which is annexed with this regulation.

**5. Payment Condition**

1. The service charges specified under the schedules which are annexed with this regulation shall be paid separately and up on the request of the services.
2. The payment to be made for every service type should be paid separately for each service.

**6. Exemption from Service Fee**

The following services shall be exempted from service fees:

፩. ተጥሎ የተገኘ ሕፃን ወይም ወላጆቹ የማይታወቁ ህፃን በአበቅራቢያው የሚገኝ ፓሊስ ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግሥት አካል ልደቱን ሲያስመዘግብ፣
፪. በአደጋ ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሞቶ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው አስከሬን ሪፓርት የተቀበለ ፓሊስ ሞቱን ሲያስመዘግብ፣
፫. የማረሚያ ቤት ኃላፊ በማረሚያ ቤት ውስጥ የሞተ ሰው ወይም የሞት ቅጣት ፍርድ የተፈፀመበት ሰው ሞቱን ሲያስመዘግብ፣
፬. በአዳሪ ትምህርት ቤት ወይም በሌላ የጋራ መኖሪያ ሥፍራ የተከሰተን ሞት የተቋሙ ኃላፊ ሲያስመግብ፣
፭. በአደጋ ምክንያት ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ሲሞቱ አደጋው ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል ከአደጋው በኋላ ሊገኝ ያልቻለ ሰው ስለአደጋው መከሰትና የጠፋው ሰው በአደጋው ወቅት ከተጐጂዎቹ ጋር አብሮ የነበረ ስለመሆኑ ባጣራው አካል በተሰጠ ማስረጃ መሠረት ሞቱ ሲመዘገብ፣
፮. ድኅነቱ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ሰው ወሣኝ ኩነት ሲያስመዘግብ፡፡

## ፯. *የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች*

፩. በዚህ ደንብ ስለተመለከቱት ሁኔታዎች የሚደነግጉ ማናቸውም ሌሎች የከተማው አስተዳደር ደንቦችና መመሪያዎች ተሽረዋል፡፡
፪. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

1. Where a police officer or any other government organ declares the birth of an abandoned child or a child whose parents are unknown;
2. Where a police who received a report, on the death of a person by accident or unknown cause whose identity is not known, declares the death;
3. Where a head of a prison declares the death of a person who died in prison or the death of a person whose death sentence is executed in the prison;
4. Where a person who is in charge of a boarding school or any other common dwelling place declares the death of a person who died in such institution;
5. If a person disappeared after several persons died simultaneously due to a calamity, and when the death of such person is registered up on the presentation of an evidence issued by the organ that has investigated the occurrence of the calamity and the presence of that person among the victims during the calamity;
6. When a person whose pauperism is being ascertained by an appropriate organ declares a vital event.

## 7. Repealed and Inapplicable Laws

1. Any other regulations and directives of the city government relating to matters provided for in this regulation are repealed.
2. Any regulation or directive, which is inconsistent with this regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**፰. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**8. <u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force upon its publication in the Negari Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of July, 2018.**

**Diriba Kuma**

**Mayor of the Addis Ababa City**

## ሠንጠረዥ አንድ

## በወሣኝ ኩነት ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር ፪/፪ሺ፰ /እንደተሻሻለ/ መሠረት ለሚሠጥ አገልግሎት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ

### ፩. ልደት

፩. ለወቅታዊ ዝገባ……………………………ብር 45.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ……………………………ብር 75.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ………………ብር 150.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 40.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት…………………………………… ብር 40.00

### ፪. ጋብቻ

፩. ለወቅታዊ ምዝ…………………………ብር 80.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………………ብር 150.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ……………ብር 200.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 60.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት…………………………… ብር 60.00

### ፫. ፍቺ

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ…………………ብር 80.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………………ብር 150.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ……………ብር 200.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 60.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት………………ብር 60.00

### ፬. ሞት

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………ብር 45.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………………ብር 75.00

## Schedule One

## Service Charges to be paid for Services Rendered Pursuant to Vital Events Registration Implementation Directive Number 2/2016 (As Amended)

### 1. Birth

1. Current registration --------------------- birr 45.00
2. Delayed registration ------------------ birr 75.00
3. Invalid registration ----------------- birr 150.00
4. Correction, renewal, verification, copy ----------------------------------------- birr 40.00
5. Certificate replacement ------------ birr 40.00

### 2. Marriage

1. Current registration ------------------- birr 80.00
2. Delayed registration ------------------ birr 150.00
3. Invalid registration ------------------ birr 200.00
4. Correction, renewal, verification, copy ---------------------------------------- birr 60.00
5. Certificate replacement -------------- birr 60.00

### 3. Divorce

1. Current registration -------------------- birr 80.00
2. Delayed registration ------------------ birr 150.00
3. Invalid registration ------------------- birr 200.00
4. Correction, renewal, verification, copy --------------------------------------- birr 60.00
5. Certificate replacement --------------------------------------------------------- birr 60.00

### 4. Death

1. Current registration -------------------- birr 45.00
2. Delayed registration ----------------- birr 75.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ……………..ብር 150.00
፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ……………..ብር 20.00
፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት…………. -ብር 20.00

፭. ጉዲፈቻ
፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………ብር 45.00
፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………..……ብር 75.00
፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ……………ብር 150.00
፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ……………..ብር 40.00
፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት……………..ብር 40.00

፮. አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………… ብር 45.00
፪. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ፣………… ብር 40.00

፯. ልጅነትን መቀበል
፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………… ብር 45.00
፪. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ፣………… ብር 40.00

ሠንጠረዥ ሁለት
በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ ዜጎች ወሣኝ ኩነት ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር ፭/፪ሺ፱ መሠረት ለሚሰጥ አገልግሎት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ

፩. ልደት
፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………ብር 400.00
፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………………ብር 500.00

3. Invalid registration ------------------ birr 150.00
4. Correction, renewal, verification, copy ---------------------------------------- birr 20.00
5. Certificate replacement ---------------- birr 20.00

**5. Adoption**
1. Current registration ------------------- birr 45.00
2. Delayed registration ------------------- birr 75.00
3. Invalid registration ------------------- birr 150.00
4. Correction, renewal, verification, copy -------------------------------------- birr 40.00
5. Certificate replacement ---------------- birr 40.00

**6. Acknowledging Paternity through Court**

1. Current registration -------------------- birr 45.00
2. Correction, renewal, verification, copy ------------------------------------ birr 40.00

**7. Accepting a Child**

1. Current registration ------------------- birr 45.00
2. Correction, renewal, verification, copy ------------------------------------ birr 40.00

**Schedule Two**
**Service Charges to be paid for Services Rendered Pursuant to Foreign Nationals Living in Ethiopia Vital Events Registration Implementation Directive Number 5/2017**

**1. Birth**
1. Current registration --------------------------------------------------------------- birr 400.00
2. Delayed registration -------------------------------------------------------------- birr 500.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ………………ብር 600.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 60.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት…………… ብር 60.00

፪. <u>ጋብቻ</u>

**ከተጋቢዎች አንዱ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ!-**

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………..ብር 600.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………………ብር 700.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ…………ብር 800.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 120.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት………………………… ብር 120.00

**ሁለቱም ተጋቢዎች የውጭ ዜጎች ከሆኑ፡-**

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………..ብር 700.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ…………………………ብር 800.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ……………ብር 900.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 160.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት……….. ብር 160.00

፫. <u>ፍቺ</u>

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ…………………..ብር 400.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ………………………ብር 600.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ…………ብር 800.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 100.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት……… ብር 100.00

3. Invalid registration ------------------- birr 600.00
4. Correction, renewal, verification, copy ---------- ----------------------------- birr 60.00
5. Certificate replacement ---------------------------- ----------------------------- birr 60.00

2. <u>**Marriage**</u>

**When either of the couple is an Ethiopian:**

1. Current registration ------------------- birr 600.00
2. Delayed registration -------------------birr 700.00
3. Invalid registration --------------------birr 800.00
4. Correction, renewal, verification, copy ---------- ----------------------------- birr 120.00
5. Certificate replacement ---------------birr 120.00

**When the couples are foreign national:**

1. Current registration -------------------birr 700.00
2. Delayed registration ------------------ birr 800.00
3. Invalid registration ------------------- birr 900.00
4. Correction, renewal, verification, copy ---------- ---------------------------- birr 160.00
5. Certificate replacement ---------------birr 160.00

3. <u>**Divorce**</u>

1. Current registration --------------------birr 400.00
2. Delayed registration -------------------birr 600.00
3. Invalid registration --------------------birr 800.00
4. Correction, renewal, verification, copy ---------- ---------------------------- birr 100.00
5. Certificate replacement ---------------------------- ---------------------------- birr 100.00

፬. **ሞት**

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………..ብር 200.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ………………….ብር 500.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ..……..ብር 600.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………ብር 60.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀት………………………………. ብር 60.00

፭. **ጉዲፈቻ**

፩. ለወቅታዊ ምዝገባ……………………..ብር 400.00

፪. ለዘገየ ምዝገባ………………………...ብር 500.00

፫. የጊዜ ገደቡ ላለፈ ምዝገባ…………….ብር 600.00

፬. ለእርማት፣ ለዕድሣት፣ ለማመሣከር፣ ለግልባጭ………………………ብር 60.00

፭. ለምትክ ምሥክር ወረቀ……… ብር 60.00

**ሠንጠረዥ ሦስት**

**ለነዋሪነት መታወቂያና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ**

፩. አዲስ የነዋሪነት መታወቂያ ለመስጠት………………………………. ብር 20.00

፪. የነዋሪነት መታወቂያ በወቅቱ ለማደስ…………………………… … ብር 20.00

፫. የዕድሣት ጊዜ ያለፈበት የነዋሪነት መታወቂያ ለማደስ……………………..…ብር 30.0

፬. የነዋሪነት መታወቂያ ከጠፋ፣ ከተቀደደ፣ ወይም በተለያየ ምክንያት ከጥቅም ውጭ ከሆነ ምትክ ለመስጠት………………………ብር 25.00

፭.በነዋሪነት መታወቂያ ላይ የፊደል ግድፈት ወይም የዕድሜ አፃፃፍ ወይም ሌላ ግድፈት ለማስተካከል ……..…………………………………ብር 25.00

4. **Death**
   1. Current registration -------------------birr 200.00
   2. Delayed registration ------------------birr 500.00
   3. Invalid registration ------------------ birr 600.00
   4. Correction, renewal, verification, copy --------------------------------------- birr 60.00
   5. Certificate replacement --------------------------------------------------------- birr 60.00

5. **Adoption**
   1. Current registration -------------------birr 400.00
   2. Delayed registration ------------------birr 500.00
   3. Invalid registration -------------------birr 600.00
   4. Correction, renewal, verification, copy ------------------------------------ birr 60.00
   5. Certificate replacement ----------------birr 60.00

**Schedule Three**

**Service Charge to be paid for Residents Identity Card and Other Services**

1. Issuance of a new residents' identity card ------------------------------------------- birr 20.00
2. Current renewal of resident' identity card ------------------------------------------- birr 20.00
3. Renewal of invalid residents' identity card ----------------------------------------- birr 30.00
4. Issuance of an identity card for the replacement of lost, torn apart or damaged ones ------------------------------------------------------- birr 25.00
5. Correcting errors of wording, age or other ------------------------------------------ birr 25.00

፯. ያላገባ አገልግሎት ለመስጠት………………..……….ብር 80.00

፯.ያላገባ አገልግሎት ለእርማት፣ ለእድሣት፣ ለማመሳከር እና ለግልባጭ አገልግሎት …………….ብር 25.0

፰.ሌሎች የነዋሪነት አገልግሎቶች ……………………………………… ብር 20.00

፱.ለሌሎች የነዋሪነት አገልግሎቶች እርማት፣ እድሣት፣ ማመሣከር እና ግልባጭ አገልግሎ ……….……………………….. ብር 20.00

## ሠንጠረዥ አራት

## ለሌሎች አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ

፩. ለቪዲዮ አገልግሎት………………….. ብር 150.00

፪. ለኤምባሲ ለሚሠጥ መረጃ አገልግሎት…………………. ብር 60.00.

፫. ለፎቶግራፍ አገልግሎት……………… ብር 100.00

፬. ለሰነድ ኮፒ አገልግሎት……………… ብር 20.00

፭. ማስረጃ የማረጋገጥ አገልግሎት………. ብር 20.00

6. Provision of unmarried certificate ---------------------------------------------------- birr 80.00
7. Correction, renewal, verification and copy of unmarried certificate service provision -------------------------------------------------- birr 25.00
8. Other services for residents ------------------------------------------------ birr 20.00
9. Correction, renewal, verification and copy of other services for residents ----------------------------------------------------------- birr 20.00

## Schedule Four

## Service Charges for Other Services

1. Video service ------------------------- birr 150.00
2. Service provision for information to be sent for an embassy --------------------- birr 60.00
3. Photograph service ------------------ birr 100.00
4. Copying of documents service ------------------------------------------------------- birr 20.00
5. Verification of evidences service ---------------------------------------------------- birr 20.00